የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

# ትንፋሽ ሲያጥር ሰበብ ፈጠራ ፤

በኢህአዴግ ሰፈር ፤ ጉልበት እየከዳ ፤ ልብ እየሸፈተ ፤ ፍርሓት እያራደ ፤ በመምጣት ላይ እንደሚገኝ ለመታዝብ እየበቃን ይመስላል ። ቃናው ተለውጧል ። መንገዱን ጨርቅ ያርግላቹ ይባል የነበረው እርግማን እንበለው ምርቃት ዛሬ አይሰማም ። የቀረው አማራጭ ትጥቅ ተጠቅሞ ተቃዋሚን ማስወገድ እንደሆነ በግልጽ ይታያል ። የሰሞኑ የኢህአዴግ መሪዎች "ኢንተርሀመዌ" ፤ "አደገኛ ቦዘኔ" ፤ "እውነተኛ ተቃዋሚ የለም". . . ወዘተ እያሉ የሚፈጥሩዋቸው ሰበቦች መሠረተ አልባና መረን የለቀቁ ማስፈራርያና ዛቻዎች የሚያመሩት ተቃዋሚን በጥይት መፋለም ወደሚለው አማራጭ እያመሩ መሆኑ
ግልጸ ነው ።

በአቶ መለስ ዜናዊ አባወራነት የሚመራው የኢህአዴግ መሪዎች የሌለውን እንዳለ ፤ ያለውን ደግሞ እንደሌለ አርገው ማናፈስ ፤ ማውራትና ማስመሰል የተካኑት ሙያ መሆኑ ከገባን ውሎ አድሯል ። ዛሬ እንደግል ንብረት አፍነው ይዘውት የነበረው ትግራይ ውስጥም ሳይቀር በጣት የሚቆጠሩ የግል ተወዳዳሪዎች በትግራይ ህዝብ ፊት ጉዳቸውን እያጋለጡ እንዲተፉ በማድረግ እያርበተበቱዋቸው ይገኛሉ ።

በዚህ ምክንያትም ፤ የኢህአዴግ መሪዎች ፤ እኛ ካልተመረጥን ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንተርሀመዌ ምልሻዎች በሩዋንዳ ቱትሲዎችና ለዘብተኛ ሁቱዎች ላይ ያደረሱት ዓይነት የዘር ማጥፋት ወንጀል ይደርሳል ብለው የአዞ እንባ እየረጩ ፤ መራጩን ህዝብ ለማሸበር ሙከራ በማድረግ ላይ ናቸው ። ህወሓት/ኢህአዴግ ተቃራኒውን ለማጥፋት ሲፈልግ አስቀድሞ የተለያዩ የፈጠራ ልጠፋዎችን በመፈብረክ ጥልቅ የማጥላላት ፕሮፓጋንዳ የማሰራጨት ልምድ እንዳለው እናውቃለን ። የዛሬ ኢንተርሀመዌ የሚል ኢህአዴግ ለተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የሰጠው ቅጽል አመጣጥም ፤ ምንጩ የኢህአዴግ ተቃዋሚን የማንበርከክ የቆየ ፍላጎት ነው ። ኢህአዴግ ተቃዋሚው የሚያቀርባቸው አማራጭ አመለካከቶችን ለመመከት የሚያስችለው ብቃት ሊፈጥር ሳይችል በመቅረቱ ፤ ተቃዋሚውን በመሳርያ ኃይል ለመፋለም መዘጋጀቱን እየነገረን ነው ። በዚህ ምክንያትም ዛሬ ተቃዋሚን ለመምታት ያስችሉኛል ብሎ ያመነባቸውን ሰበቦች ፈልፍሎ ባደባባይ እያስተጋባ ይገኛል ። ለሕግ ከማይገዛ ፤ በህዝብ ነፃ የምርጫ ድምጽ ከመተማመን ይልቅ ፤ በማታለልና በዓመጽ ሥልጣን ላይ ለመኖር ከሚሻ የሥልጣን ጥመኛ አምባገነን ኃይል ሊጠበቅ የሚቻለውም ከዓመጽ ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም ።

ኢህአዴግ እኔ ካልተመረጥኩ አገር ትበታተናለች ፤ ኢንተርሀመዌ ያደረሰው የዘር ማጥፋት ወንጀል ተቃዋሚው ኢትዮጵያ ውስጥ ያደርሳል እያለ ይገኛል ። የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታን ስንመለከት ግን የኢንተርሀመዌን ዓይነት ክስተት ሊያስከትል የሚችል ተጨባጭ ምልክት አለመኖሩን እንታዘባለን ።
በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የኢንተርሀመዌ አፈጣጠርን አስመልክተን ዝርዝር ጭብጦችን ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ባናገኘውም ፤ የኢንተርሀመዌ አፈጣጠር ከበልጂየሙ ንጉሥ ሌዎፓልድና በህዋላም በእግሩ የተተኩት የእንግሊዞች የቅኝ አገዛዝ የከፋፍለህ ግዛ ሥርዓቶች ጋር የተቆራኘ ፤ ሁለቱም ቅኝ ገዥዎች ላገዛዝ እንዲመቻቸው የሁቱንና የቱትሲን ዘሮች ለመከፋፈል የተጠቀሙበት ዘዴን ተከትሎ የመጣ መሆኑን ሳናመላክት ማለፉ አገባብ አይሆንም ። ሁለቱ ቅኝ ገዥዎች በሁለቱ ዘሮች መካከል እንደ ህዝብ ከፍተኛ ቅራኔዎች

እንዲፈጥሩ አበክረው የሠሩበት በመሆኑ ፣ የሁለቱ ህዝቦች ቅራኔ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሊሸጋገር የቻለበት ሁኔታ መፈጠሩን እናያለን ። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው ሁኔታ ሩዋንዳ ውስጥ ከነበረው ሁኔታ ጋር ለማወዳደር የሚቻልበት ምንም ዓይነት መመዘኛ የለም ። የኢትዮጵያ ሁኔታን ስንመለከት የሚፈጠሩ ቅራኔዎች በህዝቦች መካከል የተከሰቱበት ታሪክ የለም ። ያለን ታሪክ በገዢ መደቦች መካከል የተነሱ ቅራኔዎች የጦርነቶችና የእልቂቶች ምንጭ ሆነው ቢቆዩም አንዱ ገዥ መድብ ተቀናቃኙን ካንበረከከ በህዋላ ህዝብን ከህዝብ ጋር ያፋጀበት ክስተት የለም ። ይህ የሚያሳየን አገራችን ውስጥ የገዥዎች ቅራኔ እንጂ የህዝቦች ቅራኔ አለመኖሩን ነው ። ኢህአዴግ አዲስ አበባን ለመቆጣጠር በተቃረበበት ወቅት መንግሥቱ ኃይለማርያም የሰሜን ሸዋ ህዝብ ትግሬዎች መጡብህ ተነስ የሚል ጥሪ ስያስተላልፍ የሸዋ ህዝብ የመንግሥቱን ጥሪ ሰምቶ አለመዝመቱ የሚያሳየን ሀቅ በህዝቦች መካከል የሚነሳ ህዝብ ለህዝብ የመጠፋፋት ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊከሠት የማይችል መሆኑን ነው ። ስለዚህም ምንም እንኳ ከኢህአዴግ ከራሱ ጀምሮ አንዳንድ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ህዝብን ከህዝብ ጋር ለማጋጨት የሚከጅሉ ንግግሮችን ሲያደርጉ ቢስተዋሉም ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች እርስ በርስ ለመጠፋፋት ሊነሳሱ የሚችሉበት ሰበብ ለመፍጠር አልቻሉም ፣ አይችሉምም ። ከዚህ ተነስተን ስንገመግመው ፣ ባሁኑ ሰዓት የኢንተርሀመዌን ዓይነት ዘርን የማጥፋት ዘመቻ ሊጀመር ይችላል ብለን እንኳ ብናስብ ለመነሳቱ ምክንያት ሊሆን የሚችለው የሌለውና የማይታየውን ኢንተርሀመዌ እንዳለ አርጎ ሊያሳየን የሚሞክረው ኢህአዴግ ብቻ ሊሆን እንደሚችል ምንም ጥርጣሬ የለንም ። በዚህም ኢህአዴግ ተቃዋሚውን ወገን ለመምታት ከፈለገ እንደለመደበት ይግደል ፣ ይሰር ፣ ያሰቃይ እንጂ የሌለውን ሰበብ እየፈጠረ ማመኻኘት የለበትም እንላለን ።

ስለዚህም የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታና ታሪክን አዛምደን ስንመለከት ኢንተርሀመዌ የኢህአዴግ አመራር ራሱ በሚቆጣጠረው ምርጫ ቢሸነፍ ሥልጣኑን ላለማስነጠቅ እርምጃ ለመውሰድ እንዲመቸው አስቀድሞ የፈጠረው ሰበብ ከመሆን ያለፈ አለመሆኑን ለህዝቦቻችን ልናስገነዝብ እንወዳለን ። ት.ዴ.ት ይህ ሓላፊነት የጎደለው የኢህአዴግ የማጭበርበር ተግባር ለዘለቄታው የአገርና የህቦችን አንድነት የሚፈታተን መጥፎ አደጋ የሚያስከትል መሆኑ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከወዲሁ ተገንዝቦ ይህንን ሓላፊነት የጎደለውን ህዝቦችን የማፋጀት መላምት የነደፉት ወገኖች ለዚህ እጥፊ ተግባራቸው ሓላፊነቱን እንዲወስዱ ሊያስገድዳቸው ይገባል ይላል ። ከዚህም በተጨማሪ ኢህአዴግ በምርጫ ማግስት ፈጥሮ ሲያስተጋባው የቆየውን የፈጠራ ሰበብ በመምዘዝ ያለመውን የጥፋት እርምጃ እንዳይወስድ ከወዲሁ እናስጠነቅቃለን ።

ከዚህ ሌላ ባሁኑ ወቅት ከፖለቲካ ድርጅቶች በተጨማሪ ፣ የግል ተወዳዳሪዎችም በምርጫ ሂደቱ ውስጥ በመሳተፍ የኢህአዴግ ሥርዓት አልበኝነትን አምርረው በማጋለጥ የራሳቸው ተግባራዊ ፕሮግራሞችን ነድፈው ለህዝብ ይፋ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን ዜግነታዊ ግዳጅ በመወጣት ላይ መሆናቸውን ተገንዝበናል ። በዚህም እነዚህ ወገኖቻችን የጀመሩትን ትግል ከልብ እንደግፋለን ። የሚከፍሉትና እየከፈሉት ያለው መስዋእትነትን እናደንቃለን ። በዚህም ጠቅላላው ህዝባችን ለዴሞክራሲያዊያን የግል ተወዳዳሪዎችም ድምጹንና ዙርያ ምላሽ ድጋፉን እንዲለግሳቸው እናሳስባለን ።

የተደራጁ ተቃዋሚ የፖለካ ድርጅቶች ምርጫውን ሂደት አስመልክቶ ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ እንዲቋቋም ያቀረቡዋቸው ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ሊገኙ ባለመቻላቸው አንዳንዶቹ ምርጫው ውስጥ ላይሳተፉም እንደሚችሉ ግምት ውስጥ የሚገባ ሲሆን ፣ የግል ተወዳዳሪዎች ግን ይፋዊ በሆነ መንገድ ያቀረቡት ቅድመ ሁኔታ ባለመኖሩ በምርጫው ውስጥ በሙሉ ልብ ይሳተፋሉ ብለን እናምናለን ። በዚህ በምርጫው ውጤትም መልካሙን ሁሉ እንመኝላቸዋለን ። በህዝቡ ድጋፍ በሚያገኙት አርኪ ውጤት በመተማመንም የመራጩን ህዝብ አደራ ባገባቡ ለመወጣት እንዲችሉ የበኩላችንን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን እየገለጽ ፣ የህዝቡ ድጋፍ እንዳይለያቸው አደራ እንላለን ።

እንግዲህ ኢ.ህአዴግ የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ድምጹ ቢነፍገው ምን ለማድረግ እንደተዘጋጀ ነግሮናል ። አንዱን ኢ.ንተርሀመዌ ፤ ሌላው ደግሞ አደገኛ ቦዘኔ የሚል ታርጋ እየተለጠፈበት የፖለቲካ ድርጅቶችን ሆነ የግል ተወዳዳሪዎችን በማፈን የህዝብን ድምጽ በአፈሙዝ ለመዝጋት ተዘጋጅቷል ። በመሆኑም የኢ.ትዮጵያ ህዝቦች ይህንን አስቀድመው በመገንዘብ አምባገነኑን ሥርዓት ተባብረው ሳይቀብራቸው እንዲቀብሩት ት.ዴ.ት ጥሪውን ያስተላልፋል ።

የህዝብ የሥልጣን ባለቤትነት የሚረጋገጠው
በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻ ነው ! ! !
ምርጫን ማጭበርበር የህዝብን የሥልጣን
ባለቤትነት አይወክልም ! ! !

ት.ዴ.ት
ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ. ም ።